ዜና
አመዝኮ





# በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን የምግብ እጥረት ላጋጠማቸው ወገኖች አስፈላጊው ዕርዳታ በመቅረብ ላይ ነው

በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን በአለማያ እና ፈዲስ ወረዳዎች የምግብ እጥረት ላጋጠማቸው 36 ሺህ 507 ወገኖች አስፈላጊው የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ እየቀረበ መሆኑን የየወረዳዎቹ የምግብ ዋስትናና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ጽ/ቤቶች ሀላፊዎች ገልፀዋል::

የአለማያ ወረዳ የምግብ ዋስትናና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ጽ/ቤት ሀላፊ አቶ ተሾመ




ከበደ ሰሞኑን ወደሥፍራው ለተንቀሳቀሰው የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ሕዝብ ግንኙነት ቡድን እንደገለጹት የአለማያ ወረዳ ባለፈው ክረምት ዝናብ መጠንና ሥርጭት ማነስ ሳቢያ ገበሬው በቂ የመኸር ምርት ባለማግኘቱ እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወረዳው አብዛኛዎቹ ቀበሌዎች የተከሰተው ውርጭ የገበሬው የገቢ ምንጭ የሆኑትን እንደጫት የመሳሰሉ የግብርና ውጤቶችን በማጥፋቱ ከ25 ሺህ በላይ ሕዝብ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ፈላጊ ሆኗል:: እንደኃላፊው ገለፃ ይኸው የምግብ እጥረት በተለይ ከሦስት ወራት ወዲህ እየተባባሰ መምጣቱ ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ፣ ከክልሉ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ እና ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በተውጣጡ ባለሙያዎች ጥናት በመረጋገጡ በምግብ እጥረቱ ይበልጥ ተጠቂ ለሆኑ ህፃናት ፣ እናቶች እና አቅመ ደካሞች አልሚ ምግብ በፌዴራል አመዝኮ እየቀረበ ነው::

በዚህ ረገድ በወረዳው በጠቅላላው 2 ሺህ 325 ህፃናት በአካባቢው በሚገኙ የተለያዩ ጤና ጣቢያዎችና ክሊኒኮች እንዲሁም ጤና ኬላዎች ሳምንታዊ ክትትል እየተደረገላቸውና አስፈላጊው አልሚ ምግብ እየቀረበላቸው እንደሚገኝ አቶ ተሾመ አክለው ገልፀዋል::

በሌላ በኩልም በአለማያ ወረዳ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው 25 ሺህ 160 ሰዎች ለመጋቢት እና ሚያዝያ ወራት በጠቅላላው 7 ሺህ 548 ኩንታል የምግብ እህል ፣ 754 ኩንታል ቦሎቄ ፣ 252 ኩንታል ዘይት እና 792 ኩንታል አልሚ ምግብ ቀርቦ በክፈል

## በዚህ እትም ውስጥ

በሱማሌ ክልል ለተከሰተው የጎርፍ አደጋ የተሰጠው ፈጣን ምላሽ የብዙዎችን ህይወት ለመታደግ እንዳስቻለ ተገለፀ
ገጽ 3

አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምትሰጠውን የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ አጠናክራ እንደምትቀጥል ተገለፀ
ገጽ 4

የምግብ ዕርዳታ ግብረኃይል ስብሰባ ተካሄደ
ገጽ 5

በግንቦት ወር ውስጥ 672 ሺህ ኩንታል በላይ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ተመደቦ በመከፋፈል ላይ ነው
ገጽ 6

እ.ኤ.አ ለ2005 ዓ.ም ከቀረበው የዕርዳታ ጥያቄ ውስጥ 323 ሺህ 185 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ተገኝቷል
ገጽ 6

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት
ኮሚሽን ህዝብ ግንኙነት
የሚዘጋጅ
ስልክ. 529259
529262
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣ www.dppc.gov.et

ዜና አመዝኮ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዋችንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው



የምግብ እጥረት ላጋጠማቸው ወገኖች የሚያስፈልገው ዕርዳታ በወቅቱ እየቀረበ ይገኛል ።

አመዝኮ

መከፋፈሉን እና ቀሪውም ለመከፋፈል ዝግጁ መሆኑን ከአቶ ተሾመ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል።

አቶ ተሾመ እንደገለጹት በወረዳው የተከሰተው የምግብ እጥረት መጀመሪያ ላይ አሳሳቢ የነበረ ቢሆንም አስፈላጊው ዕርዳታ በወቅቱ በመድረሱ ችግሩን በቀላሉ ለመቆጣጠር ተችሏል። ከዚህም በላይ እየቀረበ ያለው ዕርዳታ ገበሬው ተረጋግቶ በአሁኑ ጊዜ እየጣለ ያለውን ዝናብ በመጠቀም በማሳ ዝግጅቱ ላይ እዲያተኩር ለማድረግ ያስቻለ በመሆኑ የዝናቡ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ በአጭር ጊዜ ውስጥ ችግሩ ሙሉ በሙሉ ይቃለላል።

በተመሳሳይ ሁኔታም በፈዲስ ወረዳ አስቸኳይ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ከ11 ሺህ በላይ የሆኑ ወገኖች የምግብ ዕርዳታ እየቀረበ መሆኑን የወረዳዉ ምግብ ዋስትናና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ጽ/ቤት ሀላፊ አቶ ንጉሤ አዱኛ አስታውቀዋል።

እንደ አቶ ንጉሤ ገለፃ የፈዲስ ወረዳ በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን ምግብ አጠር ከሆኑት ወረዳዎች በዋንኛነት የሚጠቀስ ሲሆን ያለፈው ክረምት ዝናብ በመጠንና በሥርጭት በቂ አለመሆን በቂ የመኸር ምርት እንዳይገባ በማድረጉ በዚህ ዓመት የምግብ እጥረቱ ሊባባስ ችሏል። የምግብ እጥረቱ መከሰት ከፌዴራልና ከክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተውጣጡ ባለሙያዎች ጥናት ከተረጋገጠ በኋላም ለችግሩ ለተጋለጡት ወገኖች አስፈላጊው የምግብ ዕርዳታ በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን አማካይነት እየቀረበ ይገኛል።

በዚህ ረገድ በመጋቢት ወር አስቸኳይ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው 11 ሺህ 347 ወገኖች 1 ሺህ 702 ኩንታል የምግብ እህል ፣ 170 ኩንታል ቦሎቄ እና 56 ነጥብ 65 ኩንታል ዘይት ቀርቦ መከፋፈሉን ለአብነት የጠቀሱት አቶ ንጉሤ የሚያዝያ ወር ቀለብም በተመሳሳይ ሁኔታ ቀርቦ በመከፋፈል ላይ ይገኛል ብለዋል። ከዚህም በተጨማሪ ከ1ሺህ በላይ ለሚሆኑ ህፃናት በቦኩ ከተማ የሚገኘውን ክሊኒክ ጨምሮ በወረዳዋ በሚገኙ 9 የጤና ኬላዎች ላይ አልሚ ምግብ እየቀረበላቸውና ሳምንታዊ ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል።

በሌላም በኩል የፈዲስ ወረዳ ምግብ አጠር ወረዳ እንደመሆኑ መጠን 62 ሺህ 456 አርሶ አደሮች በሴፍትኔት ታቅፈው ለኘሮግራሙ ማስፈፀሚያ የተመደበው ገንዘብ እና የምግብ ዕርዳታ ከመጋቢት ወር ጀምሮ እየቀረበላቸው እንደሚገኝ ከአቶ ንጉሤ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል።

የምግብ እጥረት ላጋጠማቸው ወገኖች የሚያስፈልገው ዕርዳታ በወቅቱ እየቀረበ ይገኛል ያሉት ሀላፊው ይኸም ገበሬው ተረጋግቶ በማሳ ዝግጅቱ ላይ እንዲያተኩርና በቀጣዩ የምርት ወቅት በቂ ምርት ተገኝቶ ችግሩ ሙሉ በሙሉ እንዲቀረፍ በማድረግ በኩል የሚያበረክተው አስተዋጽዖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም ብለዋል።

# በሱማሌ ክልል ለተከሰተው የጎርፍ አደጋ የተሰጠው ፈጣን ምላሽ የብዙዎችን ህይወት ለመታደግ እንዳስቻለ ተገለፀ



የጎርፍ አደጋው ስፋት ያላቸው ቦታዎችን ያዳረሰና በንብረት ላይ ያደረሰውም ጉዳት ቀላል የማይባል ቢሆንም በተደረገው ፈጣን የዕርዳታ አቅርቦት እንቅስቃሴ በሰው ሕይወት ላይ ሊደርስ ይችል የነበረውን የከፋ አደጋ ለመቆጣጠር ተችሏል።

ባለፈው ሚያዝያ ወር ውስጥ በሱማሌ ክልል በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች የተከሰተው የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ ሊያስከትል ይችል የነበረውን ጉዳት ለመቆጣጠር በፌዴራል መንግሥት እና በክልሉ መንግሥት እንዲሁም በአንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተሰጠው ፈጣን ምላሽ የብዙዎችን ሕይወት ከከፋ አደጋ ለመታደግ ያስቻለ እንደነበር የክልሉ ምግብ ዋስትናና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ገለፁ።

ቀላፎ ዞኖች በሚገኙ 11 ወረዳዎች የተከሰተው የጎርፍ አደጋ በአጠቃላይ 178 ቀበሌዎችን አጥለቅልቋል። በነዚሁ ቀበሌዎች ውስጥ ነዋሪ የነበሩ ከ100 በላይ ሰዎች በጎርፍ አደጋ ሞተዋል ፣ 116 ሺህ በላይ ሰዎች ደግሞ ከቤታቸው ተፈናቅለዋል ፣ ንብረታቸውም በጎርፍ ተወስዷል። በዚህ ረገድ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የተሰበሰቡ መረጃዎች 9789 ፍየሎች እና በጎች ፣ 6975 ከብቶች ፣ 3957 ግመሎች እንዲሁም 1808 ሔክታር የእርሻ መሬት እና 6478 በመጋዘን





የሱማሌ ክልል ምግብ ዋስትናና አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ ሀላፊ አቶ አብዱላሂ መህዲ አሊ እና በቢሮው የዕርዳታ ፕሮግራሞች ሀላፊ የሆኑት አቶ ረመዳን ሀጂ አህመድ ሰሞኑን ወደ ክልሉ ለተንቀሳቀሱት የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጅነት ኮሚሽን ሕዝብ ግንኙነት ቡድን ባልደረቦች በጋራ እንዳስታወቁት ባለፈው ወር የክልሉ በርካታ አካባቢዎችን ያጠቃው ከፍተኛ የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ አስደንጋጭ የነበረ ቢሆንም በፌዴራል አመዝኮ ፣ በክልሉ መንግሥት እና በአንዳንድ መያዶች በተደረገው ፈጣን የአደጋ ጊዜ ምላሽ አማካይነት በሺዎች የሚቆጠር ሕዝብን ሕይወት ለመታደግ ተችሏል።

ኃላፊዎቹ እንደገለጹት በክልሉ በጎዴ ፣አፍዴር ፣ ጅጅጋ ፣ ፊቅ ፣ ደገሀቡር እና

ተከማችቶ የነበረ እህል በጎርፍ መወሰዳቸውን ከሀላፊዎቹ መግለጫ ለመረዳት ተችሏል።

የጎርፍ አደጋው ስፋት ያላቸው ቦታዎችን ያዳረሰና በንብረት ላይ ያደረሰውም ጉዳት ቀላል የማይባል ቢሆንም በተደረገው ፈጣን የዕርዳታ አቅርቦት እንቅስቃሴ በሰው ሕይወት ላይ ሊደርስ ይችል የነበረውን የከፋ አደጋ ለመቆጣጠር መቻሉን ሀላፊዎቹ አመልክተዋል። ከዚህ አኳያ የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን በጎርፍ አደጋ በከፍተኛ ደረጃ በተጠቁት ምሥራቅና ምዕራብ ኢሚ ወረዳዎች እንዲሁም ቀላፎ ላይ ወደጎርፉ ተጠቂዎች በምድር ትራንስፖርት መድረስ በማይቻልበት ሁኔታ አስፈላጊ የሆኑትን የምግብ እና ሌሎች ቁሳቁሶች ዕርዳታ በሄሊኮፕተር በማቅረቡ ከፍተኛ የሆነ የሕይወት ማዳን ሥራ መሠራቱን ሀላፊዎቹ ጠቅሰዋል። በተመሳሳይ

ሁኔታም በቀብሪበያህ ፣ ፋፈን እና በራሱ በጅጅጋ ከተማም በጎርፍ ለተጎዱ ወገኖች በፌዴራል አመዝኮ ፣ በክልሉ መንግሥትና በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል አማካይነት ወቅታዊ የሆነ የምግብና የቁሳቁስ ዕርዳታ በመቅረቡ በአደጋው የከፋ ጉዳት አለመድረሱን አክለው ገልፀዋል።

በአደጋው አካባቢ የሚዘንብ ዝናብ የሚያስከትለው ጎርፍ ደረጃው ይለያይ እንጂ በየዓመቱ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች እንደሚከሰት የጠቀሱት የሥራ ሀላፊዎቹ ለወደፊቱ በጎርፍ አደጋ ሳቢያ የሚደርሰውን ጉዳት ከዚህ በበለጠ ፍጥነት ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ በተለይ በምድር ትራንስፖርት ለመድረስ አስቸጋሪ በሆነባቸው አካባቢዎች ላይ አስቀድሞ የአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ ምግብና ቁሳቁስ ማከማቸት የተሻለ መፍትሔ ሊሆን እንደሚችል አመልክተዋል። በማያያዝም በጎርፉ ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ያሉትን ወገኖች መልሶ ማቋቋም በቀጣይነት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው ብለዋል።

## አሜሪካ ለኢትዮጵያ የምትሰጠውን የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ አጠናክራ እንደምትቀጥል ተገለፀ



የምግብ ዋስትናን በብሔራዊ ደረጃ ለማረጋገጥ መንግሥትና ተባባሪዎቹ እያደረጉት ያለው ጥረት ውጤታማ ሆኖ በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናው እስከሚረጋገጥ ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች የምግብ እጥረት ለሚያጋጥማቸው ወገኖች አሜሪካ የምትለግሳቸውን የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች አጠናክራ እንደምትቀጥል ኮንግረስ ማይክ አስረድተዋል።

የአሜሪካ መንግሥት በኢትዮጵያ በምግብ እጥረት ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች የሚለግሰውን ዕርዳታ አጠናክሮ እንደሚቀጥል የአሜሪካን ኮንግረስ ማን ሚስተር ማይክ ሆንዳ ገለፁ።

ኮንግረስ ማን ይኸንን የገለፁት ግንቦት 30 ቀን 1997 ዓ.ም በእርሳቸው የተመራው የልዑካን ቡድን በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ተገኝቶ ከኮሚሽነር ሲሞን መቻል ጋር በተወያየበት ወቅት ነው።

ኮንግረስ ማን ማይክ ሆንዳ በዚሁ ጊዜ እንደተናገሩት በኢትዮጵያ ውስጥ ሥር ከሰደደው ድህነት ጋር በተያያዘ በየዓመቱ የሚከሰተውን የምግብ እጥረት ለማስወገድና የምግብ ዋስትናን በብሔራዊ ደረጃ ለማረጋገጥ መንግሥት በዚህ ረገድ እየተሠራበት የነበረውን የአስፈጻሚ አካል መዋቅር ከማስተካከል ጀምሮ ፣ በውሀ አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም በአካባቢ ጥበቃ እየተከተለው ያለው አቅጣጫ የሚያበረታታ ነው። ከዚህ አንፃር በአካባቢ ጥበቃ ላይ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን በአንዳንድ አካባቢዎች ተዘዋውረው መመልከታቸውን ኮንግረስ ማን አክለው ገልፀዋል።

በማያያዝም የምግብ ዋስትናን በብሔራዊ ደረጃ ለማረጋገጥ መንግሥትና ተባባሪዎቹ እያደረጉት ያለው ጥረት ውጤታማ ሆኖ በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናው እስከሚረጋገጥ ድረስ በተለያዩ ምክንያቶች የምግብ እጥረት ለሚያጋጥማቸው ወገኖች አሜሪካ የምትለግሳቸውን የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ዕርዳታዎች አጠናክራ እንደምትቀጥል ኮንግረንስ ማን ማይክ አስረድተዋል።

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሲሞን መቻል በበኩላቸው መንግሥት የምግብ ዋስትናን በብሔራዊ ደረጃ ለማረጋገጥ የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ መሆኑንና አበረታች ውጤቶችም እየታዩ መሆኑን ጠቅሰው መንግሥት ለሚያደርገው ጥረት መሳካት ደግሞ የለጋሾች ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና በአጠ

ቃላይ የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እገዛ ከፍተኛ ቦታ እንደሚኖረው ገልፀዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም አመታት ሥር ሰዶ ከቆየው ድህነት አንፃር የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ ለማረጋገጥም እንዲሁ የረጅም ጊዜና ተከታታይነት ያለው የልማት ጥረትን እንደሚጠይቅ ያመለከቱት ኮሚሽነር ሲሞን ጥረቱ ሙሉ በሙሉ ተሳክቶ ሀገሪቱ ህዝቧን መመገብ እስክትችል ድረስ ለምግብ እጥረት ለሚጋለጡት ወገኖች ከለጋሽ ሀገራትና ድርጅቶች የሚገኘው ዕርዳታ መቀጠል ያለበት ሲሆን ከዚህም ጎን ለጎን መንግሥት የሚያደርገውን የልማት ጥረት ማገዝም ከለጋሽ ሀገራትና መንግሥታት የምንጠብቀው ነው ብለዋል።

ኮሚሽነር ሲሞን በማያያዝም ኢትዮጵያ በየዓመቱ የሚያስፈልጋትን የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ከሚለግሡ ሀገሮች መካከል አሜሪካ ግንባር ቀደም መሆኗን ጠቅሰው በዚህ ረገድ በዚህ ዓመት ማለትም በአውሮጠውያኑ 2005 ዓ.ም ለአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ከተጠየቀው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 70 በመቶ የሚሆነው በተለያዩ ለጋሾችና ሀገራት ቃል የተገባ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 37 በመቶ በአሜሪካን መንግሥት ቃል የተገባና የተለገሠ መሆኑን ገልፀዋል። ምግብ ነክ ያልሆነ የዕርዳታ ፍላጎቱንም በተመለከተ ለሰውና እንስሳት ጤና ፣ ለግብርና ፣ለንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ፣ ወዘተ ከሚፈለገው ጠቅላላ ምግብ ነክ ያልሆነ ዕርዳታ ውስጥ እና እስካሁን ቃል ከተገባው ወይም ከተለገሠው ውስጥ 20 በመቶው በአሜሪካን መንግሥት ቃል የተገባና የተለገሠ መሆኑንም ኮሚሽነር ሲሞን አክለው አብራርተዋል።

ከዚህም ሌላ አሜሪካ ለአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ የምትለግሰውን ዕርዳታ ትርፍ አምራች ከሆኑ አካባቢዎች ከሀገር ውስጥ መግዛት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ኮሚሽነር ሲሞን እና ኮንግረስ ማን ማይክ ተወያይተዋል።

## የምግብ ዕርዳታ ግብረኃይል ስብሰባ ተካሄደ

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የዓለም ምግብ ፕሮግራምና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ለጋሽ አካላትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተወከሉበት የምግብ ግብረ ኃይል ስብሰባ በወቅታዊ የዕርዳታ ሥራዎች ላይ በማተኮር ሰኔ 1 ቀን 1997 ዓ.ም በአመዝኮ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተካሄደ።

በስብሰባው ላይ ከቀረበው ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው ለሚያዝያ ወር የተመደበው ቀለብ በአብዛኞቹ አካባቢዎች የተላከ ሲሆን በትራንስፖርት ችግር ፣ በከባድ ዝናብና በድልድይ መሠበር ምክንያት መዘግየት ያጋጠመበት የተወሰኑ ቦታዎች መኖራቸው ተረጋግጧል። ለግንቦት ወር በአመዝኮና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተመደበው 67 ሺህ 280 ሜትሪክ ቶን የዕርዳታ እህል በአብዛኞቹ ክልሎች ተልኮ እየተከፋፈለ መሆኑ በተገለጸበት በዚሁ ስብሰባ፣ በአፋር 65 በመቶ ፣ በድሬደዋ 30 በመቶ ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል 50 በመቶ ፣ በትግራይ 25 በመቶ ፣ በሀረሪ መቶ በመቶ የተላከ መሆኑ ታውቋል። ከአማራ ክልል ጥያቄ ያልቀረበ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል በሂደት ላይ እንደሆነ ተገልጿል።

ከዚህም በተጨማሪ የሴፍቲ ኔት ፕሮግራሞችን በተመለከተ የሚያዝያና የግንቦት ወራት እንቅስቃሴዎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

## በግንቦት ወር ውስጥ 672 ሺህ ኩንታል በላይ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ተመደቦ በመከፋፈል ላይ ነው

በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ፈላጊ ወገኖች በግንቦት ወር 1997 ዓ.ም ለሚያስፈልጋቸው ቀለብ በጠቅላላው ከ672 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት ተመድቦ መከፋፈሉ እና በመከፋፈል ላይ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል::

በዚሁ ወር ውስጥ በየክልሎች ለሚገኙ ተረጂ ወገኖች ከተመደበው 672 ሺህ 800 ኩንታል ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 599 ሺህ 480 ኩንታል በኮሚሽኑ ፣ ቀሪው 73 ሺህ 320 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካይነት የቀረበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል::

ለየክልሎቹ የሚመደበው የምግብ ዕርዳታ መጠን በየክልሎቹ እንደሚገኘው ችግር ስፋትና ጥልቀት የሚለያይ ሲሆን ፣ በዚህ መሠረት ለወሩ በድምሩ ከተመደበው 672 ሺህ 800 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ ለሱማሌ ክልል 235 ሺህ 430 ኩንታል፣ ለአፋር ክልል 100 ሺህ 920 ኩንታል ፣ ለትግራይ ክልል 126 ሺህ 70 ኩንታል ፣ ለኦሮሚያ ክልል 126 ሺህ 400 ኩንታል እና ለጋምቤላ ክልል 8 ሺህ 420 ኩንታል ፣ ለደቡብ ብሔር ብሄሰቦችና ሕዝቦች 79 ሺህ 680 ኩንታል ፣ ለሀረሪ ክልል 1 ሺህ 130 ኩንታል፣ ለአማራ ክልል 150 ኩንታል ፣ ለድሬደዋ መስተዳድር 530 ኩንታል እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል 70 ኩንታል ተመድቦ ለተረጂ ወገኖች በመከፋፈል ላይ ነው::

## ኢ.ኤ.አ ለ2005 ዓ.ም ከቀረበው የዕርዳታ ጥያቄ ውስጥ 323 ሺህ 185 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ተገኝቷል

ከዚሁ በለጋሽ ሀገራትና ድርጅቶች ከተገኘውና ቃል ከተገባው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 34 ሺህ 24 ሜ/ቶን በ2004 ዓ.ም ከነበረው የዕለት ዕርዳታ ክምችት የተላላፈ ፣ 71 ሺህ 815 ሜ/ቶን በ2004 ቃል ተገብቶ ወደ 2005 የተላለፈ ሲሆን ፣ ቀሪው 217 ሺህ 346 ሜ/ቶን በ2005 ዓ.ም ውስጥ አዲስ ቃል የተገባ መሆኑ ታውቋል::

ኢ.ኤ.አ በ2005 ዓ.ም አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ወገኖች ከተጠ የቀው 464 ሺህ 385 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ውስጥ እስከ ግንቦት 5 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ በጠቅላላው 323 ሺህ 185 ሜ/ቶን የተገኘና ቃል የተገባ መሆኑ ታውቋል::

ከዚሁ በለጋሽ ሀገራትና ድርጅቶች ከተገኘውና ቃል ከተገባው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 34 ሺህ 24 ሜ/ቶን በ2004 ዓ.ም ከነበረው የዕለት ዕርዳታ ክምችት የተላላፈ ፣ 71 ሺህ 815 ሜ/ቶን በ2004 ቃል ተገብቶ ወደ 2005 የተላለፈ ሲሆን ፣ ቀሪው 217 ሺህ 346 ሜ/ቶን በ2005 ዓ.ም ውስጥ አዲስ ቃል የተገባ መሆኑ ታውቋል::

ኢ.ኤ.አ. በ2005 ዓ.ም አዲስ ቃል ከተገባው 217 ሺህ 346 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ውስጥ የአሜሪካን መንግሥት 113 ሺህ 645 ፣ የአውሮጠ ሕብረት 45 ሺህ ሜትሪክ ቶን ፣ የዓለም ምግብ ፕሮግራም በብድር 28 ሺህ 721 ሜ/ቶን ፣ የኢጣሊያ መንግሥት በለገሠው 2 ሚሊዮን ዩሮ የሚገዛ ግምቱ 9 ሺህ ሜ/ቶን የምግብ እህል ፣ የጃጠን መንግሥት በለገሠው 2 መቶ ሚሊዮን የን የሚገዛ ግምቱ 6 ሺህ ሜ/ቶን የምግብ እህል፣ ሰዎች ለሰዎች የተባለው ግብረ ሰናይ ድርጅት 4 ሺህ 928 ሜ/ቶን፣ የእስፔይን መንግሥት 845 ሜ/ቶን የአየርላንድ

መንግሥት 815 ሜ/ቶን ፣ የኖርዌይ መንግሥት 2 ሺህ 616 ሜ/ቶን ፣ የካናዳ መንግሥት 5 ሺህ 678 ሜ/ቶን እና የግብፅ መንግሥት 64 ሜ/ቶን የምግብ እህልና አልሚ ምግብ ለግሰዋል። እ.ኤ.አ ከ2004 ዓ.ም ከነበረው ክምችትና ቃል ተገብቶ ከተሸጋገረው እንዲሁም እ.ኤ.አ በ2005 ቃል ከተገባው 323 ሺህ 185 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 245 ሺህ 791 ሜ/ቶን የምግብ እህል ፣ 36 ሺህ 232 ሜ/ቶን አልሚ ምግብ ፣ 13 ሺህ 723 ሜ/ቶን ዘይት ፣ ቀሪው 27 ሺህ 379 ደግሞ ጥራጥሬ መሆኑ ታውቋል።

በሌላም በኩል በስዊድን የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች የለገሱትን 185 ሺህ የስዊድሽ ክሮነር ወይም ብር 220 ሺህ 540.77 የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ተረከበ።

ኢትዮጵያውያኑ ከኢትዮጵያ ወዳጆች ጋር በመሆን የለገሡት ይህ ገንዘብ በስዊድን ስቶክሆልም በሚገኘው የኢፌዴሪ ኤምባሲ አማካይነት ግንቦት 1 ቀን 1997 ዓ.ም ወደ ኮሚሽኑ የባንክ ሂሳብ ገቢ ተደርጓል።

ኮሚሽኑም በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ገንዘቡን ለሚያካሂደው የዕርዳታ ሥራ እንደሚያውለው አረጋግጦ በተረጅ ወገኖች ስም ምስጋናውን አቅርቧል።